# ሾላ ቢረግፍ ከዛፉ አይርቅም

(አገሬ አዲስ)

ጊዜውን ተከትሎ በሚከሰት የውስጣዊ ለውጥ ወይም በሃይለኛ ንፋስ፣ዝናብና በረዶ ምክንያት ከተንጠለጠለበት የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ተነጥሎ የሚወድቅ ፍሬ ከዛፉ ሳይርቅ በዙሪያው ባለው መሬት ላይ እንደሚያርፍ የታወቀ ነው።ምንም እንኳን ከግንዱ ቢነጠልም ዛፉ ከተሸከማቸው ካልረገፉት መሰሎቹ በመልክና በጣሙ የተለዩ አይሆንም።ልዩነቱ የቦታ ብቻ ነው።
ሰዎች በቦታ ቢለያዩም ያላቸውን በመልክም ሆነ የአስተሳሰብ ዝምድናና መመሳሰል ለመግለጽ ያገሬ ሰው በሾላ ፍሬና በግንዱ አስመስሎ በተረትና ምሳሌ" ሾላ ቢረግፍ ከዛፉ አይርቅም!"በማለት ሲገልጸው ኖሯል። ታዲያ ይህን የሚያበስር ሁኔታ በቅርቡ በአገራችን የፖለቲካ ውጣውረድና አሰላለፍ ለመታዘብ ችለናል።

ዛፉን እንደ ድርጅት ፍሬውን አንደ አባላቱ ብናዬው በተለያዬ ጊዜ በልዩልዩ ምክንያት ከድርጅቱ ተነጥሎ የሚወጣ እንደሚኖር የታዬና የማይታበል እውነታ ነው።በአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ በሚነሳው ውስጣዊ ነውጥ በሚፈጠር አለመግባባት በአካሄድና በስልት ወይም በስልጣንና ጥቅም ወይም በድርጅቱ ላይ በሚደርስ ችንፈት አባላቱ እንደሚባረሩ ወይም እንደሚነጠሉ በተደጋጋሚ አይተናል።ሆኖም ግን ከድርጅት ቢወገዱና ወይም እራሳቸውን ቢያርቁ በአብዛኛው እንደታዬው መራራቁ የአካል እንጂ የአስተሳሰብና የዓላማ ልዩነት አይሆንም።በዓላማ ላይ ልዩነትማ ቢኖር ኖሮ ከመጀመሪያው የድርጅቱ መስራችና አባል ባልሆኑም ነበር።ስለሆነም ምናልባት ከጊዜ በኋላ ሁሉም ተሰልፎበት የነበረውን ድርጅት ለአደጋ የሚያጋልጥ ችግር ቢፈጠር ይቅር ለእግዜር ተባብለው ሊሰባሰቡ ይችላሉ። ይህንን ሂደት በሰሞኑ ለማዬትና ለመስማት ችለናል።ህወሃት የተባለውን አገር አጥፊ ድርጅት የፈጠሩና ከተፈጠረም በኋላ ተሰግስገው በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ብዙ ውድመትና ወንጀል የፈጸሙ አባላት በአሁኑ ጊዜ እናት ድርጅታቸው ቀውስ ውስጥ ሲነከርና ለአደጋ ሲጋለጥ በሆነ ባልሆነው ምክንያት ተለያይተው ከቆዩ በኋላ የነበረ ልዩነትና ቂማቸውን ወደጎን አድርገው ህዋሃትን ለማዳን"ባለ አደራ" በሚል መርሆ ዙሪያ በመረባረብ ላይ ናቸው።

በየምክንያቱ ከወያኔ ተነጥለው የቆዩት አባላት፣የአካል ጉዳተኞች ሳይቀሩ በአገር ቤትና በውጭ አገር ለመሰባሰብና በዚህ ፈታኝ ወቅት ከድርጅታቸው ጎን ለመሰለፍ ደፋ ቀና እያሉ መሆናቸው ሾልኮ የወጣው መረጃ ያረጋግጣል። የዚህ ስብስብ አስተባባሪና ፊታውራሪው ስብሃት ነጋ የተባለው አንጋፋ የወያኔ ወንበዴ መሪ ሲሆን፤ከሱም ጋር ሆነው የሚያስተባብሩ በአሜሪካ፣በአውሮፓና በመካከለኛው ምስራቅ በስደተኛ ስም የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን መረጃው ጠቁሟል።ከነዚህ መካከል በግንባር ወጥተው ወያኔን ለመታደግ ከሚሯሯጡት መካከል በሥልጣን ላይ ተቀምጦ ብዙ ወንጀል የፈጸመው ጀኔራል ጻድቃን አንዱ ነው።ይህ ጀኔራል ብዙ አትዮጵያውያን ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡበትን የኢትዮጵያ መሬት የሆነውን ባድሜን እንደ ህወሃት የግል ሃብት አሳልፎ ለመስጠትና በሁለቱ የወንበዴ ድርጅቶች መካከል የነበረው የጥቅም ግጭት ተወግዶ በጋራ የነበራቸውን ጸረ ኢትዮጵያ ግንባር ለማደስ እንዲችሉ ከመሰል አጋሮቹ ከኤርትራውያን ጋር በመወያዬት ላይ ነው።ሌሎቹም እንዲሁ ወያኔን እንቃወማለን በማለት ለተመሳሳይ ዓላማ የትግራይ ጎሰኛ ድርጅቶች ያቋቋሙት የወያኔ መስራቾች በአሳሳች ስልት ወገናዊነትን በሚያንጸባርቅና ወያኔን ለማዳን የስርዓቱን ሕገ-መንግሥት ተቀብለን እንደራደር በማለት ከሌሎች ጎሰኛ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የድርድር ሰነድ በማዘጋጀት ላይ እንደሆኑ ተደርሶበታል።
የወያኔ መዳከምና መውደቅ እንቅልፍ የነሳቸው የወያኔ ደጋፊዎች የሆኑትን የትግራይ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን ለወያኔ አጋር ለሆኑት የጎሳ ድርጅቶችም ጭምር ነው።እነዚሁ ድርጅቶች ወያኔ የሚመራበትን ሕገመንግሥት አብረው ያረቀቁ፣አትዮጵያ የምትባል አገር ሌሎቹን ጎሳዎች በነሱ አጠራር "ብሔር ብሔረሰቦች" በመውረር የተፈጠረች አገር በመሆኗ ተበታትና ነጻነታችንን እንቀዳጅ ብለው የሚያምኑ ናቸው።በዚህ እምነታቸውም ሥልጣንና ጥቅም እስከለያያቸው ድረስ ከወያኔ ጋር አብረው በሕዝቡ ላይ ግፍ የፈጸሙ ወንጀለኞች ናቸው።ወያኔ ቢወድቅና ከሥልጣን ተባሮ በዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ስርዓት ቢተካ አገኘን የሚሉት መብት ማለትም ቋንቋን መሰረት ያደረገው ክልልና በአንቀጽ 39 ስር የተቀመጠው የመገንጠል መብት ሊሰረዝብንና ልናጣው እንችላለን ከሚል ስጋት የተነሳ ያለውን ሕገ መንግሥት ተቀብለን ከወያኔ ጋር ተደራድረን ስርዓቱ እንዲቀጥል እናድርግ ብለው በመሯሯጥ ላይ ናቸው።አገር ለማዳን የተጨነቁ መስለው ስጋታቸው ግን ከላይ

የተገለጸው ከወያኔ ጋር የሚወድቀው አብረው የነደፉትና የሚያምኑበት ኢትዮጵያን በኃሳ ለመበታተን የሚረዳው ሕገ-መንግሥት ብቻ ነው።
የሁሉም ጭንቀትና ሽብር አሁን በሚታዬው አዝማሚያ አትዮጵያ የሚለው መንፈስ ካንሰራራ ቦታ እንደማይኖራቸው ስላወቁት ወያኔ ጋር ያላቸውን ቅራኔ ወደጎን ትተው መቀራረቡን መርጠዋል።በዚህ ቀውጢ ሰዓት ከዓላማ አጋራቸው ጎን ለመሰለፍ ዝግጁ ሆነዋል።አንዳንዶቹ የወያኔ የዓላማ ቤተሰቦች አቋማቸውን በቅርቡ በአውሮፓ ከተማዎች በብራሰልስና በፍራንክፈርት ከተማ በተካሄዱት ስብሰባዎች ላይ ይፋ አድርገውታል።

በስም ተቃዋሚ ፤በተግባር ደጋፊ የሆኑ የትግራይ ድርጅቶች ወያኔ የአጎራባች ክ/ሃገሮችን መሬት እየቀማ ሕዝብ የማፈናቀሉንና የትግራይን ወሰን የማስፋፋቱን ወንጀል ሲያወግዙ አይሰማም።አይቶ እንዳላዬ ያልፉታል። የክፍለሃገር ወሰን መጥበብና መስፋት፣መዋዋጥ ያለና የቆዬ ልማድ ነው በማለት በሕዝቡ ጥያቄና ፈቃድ ያለተከናወነውን ወረራ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት ይሞክራሉ።አልፎ ተርፎም የትግሬ የበላይነት የለም ብለው ሸንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ። የመከላከያውን፣ የኤኮኖሚውንና የፖለቲካውን መድረክ ከታች እስከ ላይ ማን እንደሚቆጣጠረው ጸሃይ የሞቀውን አገር ያወቀውን ጉዳይ የለም ብለው ይክዳሉ።ወያኔ የትግራይ ተወላጆች የተሰባሰቡበት ድርጅት አይደለም ካልተባለ በስተቀር አባባላቸው ውሃ አይቋጥርም።የወያኔን የበላይነት ሲባልም የትግራይ ተወላጆች የፈጠሩትና የሚቆጣጠሩት ድርጅት መሆኑን ለማሳዬት እንጂ እያንዳንዱ የትግራይ ተወላጅ በሌላው ላይ የበላይና ተጠቃሚ ሆኗል ለማለት አይደለም።

ወያኔን የተቃወመ ሁሉ አጋር ይሆናል የሚለው ፈሊጥ ጅልነት ነው። የጀርባ ታሪኩ ምን ይመስላል?ወያኔን ለምን ተቀላቀለ፣ ለምንስ ዓላማ ተቃወመ? ብሎ መጠየቅ ከዳግም ጥፋት ያድናል።ከሳት ወደ እረመጥ ላለመውደቅ በአንክሮ ማዬት ተገቢ ነው።የጎሳ መርዝ የቀመመ ቡድን ወይም ግለሰብ ከልቡ ጎሰኝነትን ይታገላል ማለት ዘበት ነው።አነሳሱ ለጥፋት የሆነ ሰውና ቡድን ለበጎ ነገር አይሰለፍም።ቢሰለፍም ቀን እስኪያመቸው ድረስ የሚረጨውን መርዝ በድብቅ ተሸክሞ ሊሆን ይችላል፤ ሁኔታው ሲፈቅድለት አንገቱን ቀና ማድረጉ አይቀርም፤ስለሆነም ቦታና ዕድል መስጠት ትልቅ ስህተት ነው። የጎሰኞች አንዱ አመላካች የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚግባባበትን ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛን ወደጎን ትተው በየስብሰባው ላይ ለሚያቀርቡት ጽሁፍ በውጭ አገር ቋንቋ በተለይም በእንግሊዝኛ መጻፉን መምረጣቸው ነው።ይህ አማርኛንና አማራውን ከመጥላት አቋማቸው የመነጬ እንደሆነ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል።ባይሆንማ ኖሮ ለኢትዮጵያውያን የሚያስተላልፉትን መልእክት ለምን በእንግሊዝኛ ይጽፉ ነበር?አማርኛ አያውቁም እንዳይባል የተካኑት ቋንቋ ነው።አማርኛን መናገር የሚፈልጉት ቤተመንግሥት ሲገቡ ብቻ እንደሆነ ያዬነው ነው።
ጥፋቱን አምኖና ተጸጽቶ ይቅርታ ጠይቆ የሚመጣው ተራ አባልና ደጋፊ ከሌላው አክራሪ ወያኔና የዓላማው ነዳፊ ከሆኑት በተለዬ ዓይን መታየት ይገባዋል።ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ተብሎ ለችግር እንዳይጋለጥ መከላከሉ ተገቢ ነው። በሱ ትብብር ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች ለመሰብሰብ ይቻላል።ሆኗልም።የትግራይን ሕዝብና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን ትልቅ ሚና ሊጫወት የሚችል ስለሆነ መገፋት አይኖርበትም።

በጽሞና መታዬት ያለበት ሌላው ጉዳይ ሁሉንም የትግራይ ተወላጅ በወያኔ አይን መፈረጅና ማዬት እንደማይገባ ነው።ብዙ የትግራይ ተወላጆች ከጅምሩ ጀምሮ ወያኔን በመቃወማቸው በግፍ ተገለዋል፣ታስረዋል፣ተሰደዋል። እስከ አሁንም ድረስ በትግራይ ውስጥ አንጀታቸው እያረረ ለመቃወም አቅም አጥተው ቀን የሚጠብቁ ብዙዎች ናቸው።የአገራቸው የኢትዮጵያ መበታተን የሚያሰጋቸው የትግራይ ተወላጆች ቁጥር በጥቅምና በባዶ ፕሮፓጋንዳ ተደልሎ ወያኔን ከሚደግፈው የትግራይ ተወላጅ ቁጥር በላይ ነው።የቀን ጉዳይ ነው፤ትግሉ እየጠነከረ ሲመጣ የፍርሃት ድባቡን ጥሶ ከሌሎቹ ወገኖቹ ጋር ለለውጥ ይሰለፋል።አብዛኛው የትግራይ ክ/ሃገር ተወላጅ እናት አገሩን ጥሎ፣ትግራይን ገንጥሎ ከኤርትራ ጋር በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ወይም በባርነት ለመኖር የሚሻ አይደለም።ለዚያ የባርነት ሰንሰለት የሚጎትቱትን ይታገላል እንጂ የክልሌ ልጆች ብሎ አይምራቸውም።

ሌላው በዚህም በዚያም ብዬ ሥልጣን እይዛለሁ ብሎ ከሁሉም ጋር አይኑን ሳያሽ ዓመት የማይቆይ ውል የሚፈራረመውና በየወንዙ የሚማማለው፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ስም ድጋፍና ገንዘብ የሚሰበስበው የግንቦት ሰባት አመራርም የነጻነት አውጭ ነን ከሚሉት አጋሮቹ ጋር ሆኖ የወያኔን ሕገመንግሥት መቀበሉን ይፋ ማድረጉ አይዘነጋም። በኤርትራ ውስጥ መሽጎ አካሂዳለሁ የሚለው የትጥቅ ትግል የታዬ ውጤት ባለማምጣቱና የሻእብያና የወያኔ መቀራረብ ሲያስጋው ማርሹን ለውጦ በሰላማዊ ትግል አምናለሁ የሚል ቅኝት ማሰማት ጀምሯል።እንዴት ሲባል ዱሮም እኮ ሁለገብ ትግል እንደምናካሂድ

ገልጸናል ይለናል።በዚህም ሆነ በዚያ ሥልጣን አገኛለሁ ብሎ የሚቋምጠው ግንቦት ሰባት ቢሳካለት ስልጣኑን ጠቅሎ ለዳግመኛ ወያኔ መሰል የጎሰኞች ስርዓት መስፈን የሚዳዳ እንጂ መሰረታው የሆነ ከጎሰኞች ነጻ የሆነ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚታገል አለመሆኑ ከሰበሰባቸው አጋሮቹ ማንነት ለመረዳት ይቻላል። ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የጠራ አቋም የለውም።ይባስ ብሎም አንዳንዶቹን በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የከረረ አቋም አላችሁ ያ ደግሞ የሰበሰብኳቸውን ስለሚበትንብኝ አብሬያችሁ አልሰራም በማለት ለኢትዮጵያ አንድነት መቆምን እንደ ወንጀል የሚያይ ድርጅት ነው። ለግንቦት ሰባት የኢትዮጵያ አንድነት ማለት የተገንጣይና የጎሰኞች አንድነት ማለት ነው።ከነሱ ውጭ ኢትዮጵያ ትኖራለች ብሎ አያምንም።አያስብምም።ለግንቦት ሰባትና ለጎሰኞቹ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ፣ስለእረጅም ዘመን አኩሪ ታሪኳ ማውራትና ማውሳት ኋላ ቀርነት ነው።ለነሱ ዘመናዊነትና ዴሞክራት መሆን ማለት የጎሰኞችን እምነትና ዓላማ መቀበልና እውቅና መስጠት ነው።በዚህ ድርጅት ውስጥ የተሳተፉ፣የገንዘብና የሞራል ድጋፍ የሚሰጡ፣ወያኔ ተወግዶ ለኢትዮጵያ ብሩህ ቀን ይወጣል የሚል ምኞትና ፍላጎት ያላቸው ብዙ አገር ወዳዶች እንዳሉ አይካድም።” ደህና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ” ሆኖባቸው እንጂ የተሻለና ተስፋ የሚጣልበት ሀይል ቢመጣ ከግንቦት ሰባት ጉረኖ የማይወጡበት ምክንያት አይኖርም። ዳግም አገራቸውን ለጎሰኞች ስርዓት አሳልፈው አይሰጡም።

ይኸው ግንቦት ሰባት የሚሰራው ትያትር አያልቅበትም። ሰሞኑን ከጥቂት አጋሮቹ ጋር ሆኖ ያረቀቀውን የሽግግር ሰነድ በሁሉም የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ስም በአውሮፓ ህብረት ፓርላማ ውስጥ አባል በሆኑት ደጋፊው በወ/ሮ አና ጎሜዝ የስራ ቢሮ ውስጥ ባደረገው ስብሰባ ይፋ አድርጓል።በአና ጎሜዝ ቢሮ ውስጥ የተደረገውን ስብሰባ በአውሮፓ ፓርላማ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የተደረገና ህብረቱም እውቅና የሰጠው ለማስመሰል የተሰራጨው ወሬ የተለመደው ድራማ አካል መሆኑ ለብዙሃኑ ስውር አይደለም።

በሌላውም ጎራ የውጭ አገር መንግሥታት በተለይም አሜሪካ በስልጣን ላይ ያስቀመጠው የወያኔ ቡድን ለመውደቁ ሲንገዳገድ ለማዳን እንደ ዛሬ ሃያሰባት ዓመቱ ተመሳሳይ አሻጥር ለኢትዮጵያ የተቆረቆሩ በሚመስል ሽፋን የሽግግር መንግስት በወያኔና በተወሰኑ ተቃዋሚዎች ተሳትፎ እንዲቋቋም ኸርማን ኮህን በተባለው መሰሪ አስተባባሪነት መሰናዶውን ቀጥሏል። የአውሮፓ መንግሥታትም ከዚህ የተለዩ ፍላጎት የላቸውም።በአንድ በኩል ለወያኔ መራሹ መንግሥት የገንዘብና የዲፕሎማሲ ድጋፍ እየሰጡ በሌላው በኩል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸውን ጎሰኞች እያጠናከሩ ነው።ስልታቸው ” ሁለት ባላ ትክል አንዱ ቢሰበር በአንዱ ተንጠልጠል” ነው።ፍጹም አገር ወዳድና ነጻነቱን አሳልፎ የማይሰጠውን አይወዱትም፤ያርቁታል፤ቢጠፋም ፍላጎታቸው ነው። በ 83 ቱ የሽግግር ተብዬው ወቅት የፈጸሙትን አሻጥር አሁንም ለመድገም በድፍረት እየተንቀሳቀሱ ነው።

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆኑትም ግብጽ፣ሱዳንና ሌሎቹ የአረብ አገሮች እንዲሁ አክራሪና ለነሱ ጥቅም የቆሙትን ድርጅቶች በመደገፍ አገራችን እንድትበታተን የሚያስፈልገውን የገንዘብና የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ በማፍሰስ ላይ ናቸው።

የአገር ወዳዱ ተግባር ምን መሆን አለበት?

ማንኛውም የአገሩን መበታተን የማይሻ ዜጋ በዚህ ፈታኝ ወቅት ከላይ የተገለጹት ሃይሎች ዓላማቸው እንዳይሳካ ተባብሮ በአንድ መስመር ማለትም አገር በማዳኑ መስመር መሰለፍ ይኖርበታል።የጎሳን ፖለቲካና ፖለቲከኞች በቃችሁ ሊላቸው ይገባል። የውጭ መንግሥታትን በተለይም የአሜሪካንን መንግሥት ባገራችን ጉዳይ ወሳኞች መሆን እንደማይችሉና ያለፈው ደባ እንደሚበቃ ሊነግራቸው ይገባል።ለወያኔ የሚሰጡትን ማንኛውንም አይነት ድጋፍ እንዲያቆሙ ማጠዬቅና አቋሙን በግልጽ ማሳወቅ ይኖርበታል።የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ለውጥ ወያኔና ደጋፊዎቹ ተወግደው መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ እንጂ እነሱ የሚደግፏቸው የተወሰኑ ቡድኖች ወደ ስልጣን የሚወጡበት የጥገና ለውጥ እንዳልሆነ ድምጹን ከፍ አድርጎ ሊነግራቸው ይገባል።

በውጭ አገር የሚገኘው አገር ወዳድ በየጊዜው በስብሰባ የሚያወጣውን መግለጫ በተግባር መተርጎም ያለበት ጊዜው አሁን ነው።ለዚያ ደግሞ አገር አድን ግንባር ፈጥሮ ትግሉን በመሬት ላይ ከሚታዬው ከአገር ቤቱ ሕዝባዊ ትግል ጋር ማያያዝ ይኖርበታል።አሁን ያለንበት ጊዜ ከመጨረሻው ሰዓት ላይ ነው።በዚህ የመጨረሻ ሰዓት እንዳለፈው ጊዜ እርስ በርሳችን የቃላት ግብ ግብ የምንገጥምበት ወይም የድርጅት ዝና፣የበላይነትና ጥቅም የምናሳድድበት አይደለም፤ያ የድሎት ፖለቲካ

ነው።አሁን የተግባርና የፈተና ወቅት ነው። የአገራችንን አንድነትና ነጻነት በማስከበር የባዕዳን መጨፈሪያ እንዳትሆን፣ በጎሰኞች ክንድ ጥቃት የሚደርስባቸውን ወገኖቻችንን ለማዳንና፣ የአገር ቤቱ ሕዝባዊ ትግል በጎሰኞች እንዳይጠለፍ ለማድረግ ተደራጅቶ መከላከል ይገባል። የጎሳ ፖለቲካንና ጎሰኞችን የሚቃወመው በአገር ቤትና በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊያዊ የአንድነት ግንባር መፍጠር ይኖርበታል።የግንባሩ መርሆ '' አገርህን አድን '' ነው። ለዚህ ዓላማ የሚካሄደው ትግል አመርቂ ውጤት እንዲያመጣ የሚያስፈልገውን ዝግጅትና የአቅም ግንባታ በተለይም የገንዘብ ተፋሰስ ማጎልበት ተገቢ ነው።በግንባሩ የሚመራ አንድ ብሔራዊ አስተባባሪ አካል መፈጠር አለበት። ያ አካል ትግሉን የማቀናጀትና በሽግግር ወቅት ክፍተት እንዳይኖር ሚና ሊጫወት ይችላል።

ፖለቲካ ሳይንሳዊ ፍልስፍና ነው።ፖለቲካ በጎሳና በቋንቋ የሚለካና የሚቀመር አይደለም።በህብረተሰብ ኑሮና ስርዓት፣ በአንድ አገር ነጻነትና ህልውና ላይ የጋራ የሆነ አመለካከትና ራዕይ የሚነደፍበት ሳይንስ ነው።ፖለቲካ በልዩ ልዩ ያመለካከት ዘርፎች ይተረጎማል።በዴሞክራሲ፣በሶሻሊስት፣በሊበራል፣በሶሻል ዴሞክራሲ…ወዘተ።እነዚህ አመለካከቶች ደግሞ አገራዊነትና አለምአቀፋዊነት እንጂ የጎሰኝነትና ክልላዊነት ጸባይና መሰረት አይኖራቸውም።እንደ አገራችን የአማራ ዴሞክራሲ፣የትግራይ ዴሞክራሲ፣የኦሮሞ ዴሞክራሲ የዚህ ወይም የዚያ ጎሳና አካባቢ ሕዝብ ዴሞክራሲ ተብሎ በቅንጭብ አይቀርብም።በጎሳ ተዋረድ በዴሞክራሲ ስም የሚቋቋም የፖለቲካ ድርጅት ከጎሳው ውጭ ስለሚኖረው ሕዝብ አይጨነቅም።ስለሆነም አግላይና በተፈጥሮው ጸረ ዴሞክራሲና ኢስብአዊ ነው።አሁንም በአገራችን የምናየው በኢህአዴግ በተባለው የዴሞክራሲ ጃንጥላ ስር የተሰገሰጉት የጎሳድርጅቶች የሚፈጽሙት ወንጀል የዚህ ማስረጃ ነው።ዴሞክራሲን በጎሳ ከተረጎምነው በአገራችን ከሰማንያ በላይ የሚሆኑ እርስ በርሳቸው የሚጋጩና ሕዝቡን የሚያጋጩ የጎሳ ዴሞክራቲክ ፓርቲዎች ይኖራሉ ማለት ነው።እውነተኛ ዴሞክራሲ ምህዳሩ የሰፋና ለብዙሃኑ ጥቅም የሚቆም፣ብዙሃኑም የተሳተፉበት አገራዊና ዓለም አቀፋዊ አላፊነት የሚሰማው የፖለቲካ አመለካከት ነው።

ልብ ያለው ልብ ይበል!ጅብ ከሄደ…እንዳይሆንብን ዛሬውኑ ተባብረን እንነሳ። አገራችንን ከአስመሳይ ተኩላዎችና ከወያኔ ባለአደራዎች እናድን!!

አገሬ አዲስ